# ሰላማዊ ሰልፍ የማካሄድ መብት በኢትዮጵያዊው ንጉሥ ዳዊት ተፈቅዶ የተጀመረ እንጂ ከፈረንጆች የተቀዳ አይደለም !!

**ጌታቸው ረዳ** (www.ethiopiansemay.blogspot.com)

## ክፍል ፩

የዘመናችን የፈረንጅ የሥራ ውጤት የሆኑት 'ባንቡላ ወያኔዎች' (mannequin-dummies) በአፄ ምኒሊክ እና በአፄ ዮሐንስ ዘመን በትግሬና በሸዋ አማራ እየቆዘሙ "የጎሳ ፈረስ ጎታቾች ሆነው" በዚህ ዘመን ማየት እጅግ የሚቀፍ ማሃይምነት ከመሆኑ አልፎ ምንኛ ጨቅሎችና የማያምሩ የፈረንጅ ባንቡላዎች አንደሆኑ ስንገነዘብ የለከፋቸው ዛር ምንኛ ጨካኝ አንደሆነ መመለክት አስችሎናል። ዲሞክራሲ ከግሪኮች፤ ዲሞክራሲ ከወያኔዎች ዲሞክራሲ ከአሜሪካኖች ወደ ኢትዮጵያ ምድር መጣ እየተባለ የሚነገር የሐሰት ማስታወቂያ (ከመርሻል) ምንኛ የሚያስጣላ ያላዋቂነታችን እርከን አንደሆነ ከዚህ በታች የተጻፈው ዘገባ ይነግረናል።

ከዚህ በታች የሚቀርበው መረጃ "ጥንታዊ የኢትዮጵያ የሰላም ጥበቃ ታሪክ (ከቅራት- ዘመናዊ ፖሊስ) ከተባለው መጽሓፍ በሊቁ ደራሲ "አእምሮ ንጉሴ" ከተጻፈ መጽሐፍ የተገኘ መረጃ ነው። ደራሲው ይህንን መጽሐፍ ለመጻፍ የፈጀባቸው ጊዜ ከሃያ ሁለት አመት በላይ ነው። መጽሐፉ ለማዘጋጀት መረጃዎቹን ለማግኘት በኢትዮጵያ ምድር በሚገኙት ገዳማት እና ቤተክርስትያናት እየዞሩ በግዕዝ ከተጻፉ መጽሐፍት ውስጥ የቀዱት መረጃ ነው። መጽሐፉ ከተለያዩ የዘመኑ ደራሲዎች በግዕዝ የተደረሱ ዘገባዎችን ወደ አማርኛ በመተርጐም ቀጥተኛ ትርጉሙን ነው ያቀረቡልን። መጽሐፉ የታተመው በ፪ ሺህ ዓ.ም ኢትዮጵያ ውስጥ ነው።

ደራሲው በመጽሐፋቸው እንደገለጹት ከዚህ መጽሐፍ በፊት "የሰላም ዘብ የፖሊስ ጥንት ታሪክ" የተባለ መጽሐፍ ሲያዘጋጁ ጥቂት ግለሰቦች ለማደናቀፍ ከመሞከራቸው በላይ የሞራል ውድቀት እንዲደርስባቸው ያልፈነቀሉት የሴራ ድንጋይ አንዳልነበረ እና አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን ደራሲዎች የቅድመ አያቶቻችን የጥንት ስራዎቻቸውና ኢትዮጵያ እንዴት አንደተገነባች አንዳይገለጹ እንቅፋት የሆኑ አንዳንድ ጠማማ ዜጎች አንደነበሩ ገልጸዋል (ሳንሱር ማለታቸውን ነው)። ያ የመጀመሪያ መጽሐፋቸው ሲጽፉ በወቅቱ የነበሩ ያገሪቱ አንዳንድ ወታደራዊ መኰንኖች፤ እና ደራሲያን (አንደ እውቁ አሥረስ የኔሰው) የመሳሰሉ አንደ አርበኛው ራስ እምሩ ሃይለስላሴ የመሳሰሉ የመጽሐፉን ረቂቅ አንብበው አስገራሚ የድጋፍ በመቅድሙ አስተያየተቻው አስፍረውበታል።

በግሌ ለደራሲው አስተዋጽኦ ማድረግ ብችል የሚከተለው ምዕዳን ለዜጎች ወንድሞች እና እህቶች ማስተላለፍ ነው። ይኸውም ፤ መጀመሪያው መጽሐፍም ሆነ ሁለተኛው መጽሐፋቸው ለማግኘት በቀላሉ ለማግኘት የሚቸግር ቢመስልም አሁንም አገር ውስጥ ማግኘት እንደሚቻል እገምታለሁ። ኢትዮጵያዊነት መንፈስ በተለያዩ ቅጥረኞችና ማይሞች ተሰብሮ ዜጎች ቅናታቸውን ፈትተው ለአገር አፍራሶች ተመችተው ያሉትን ዜጐች ታሪካቸውን እና ማንነታቸውን የሚያውቁበት መስተዋት/ማሕደር የመጀመሪያውም ሆነ የሁለተኛው መጽሐፋቸው ዜጎች አፈላልገው እንዲያነብቡት በተቻለኝ መንገድ ለዜጎች በማስተዋወቅ አስተዋጽኦ ለማድረግ ነው ይህ ሐተታ ለመጻፍ የፈለግኩት።

በዚህ ሁለተኛ መጽሐፋቸው መግቢያ ውስጥ ድክመታችንን እንዲህ ሲሉ ይገልጻሉ።

"ኢትዮጵያ ጥንታዊ ታሪክና ሥልጣኔ የነበራት አገር ናት። ለዚህም ነው ብዙ የውጭ አገር ምሁራን ጥንታዊ ታሪኳን ለመመርመር የተገደዱት።...... "የቀድሞ ሊቃውንት ከሃይማኖት መጽሐፍት በቀር ሌላ ጠቃሚ ነገር አላቆዩልንም የሚል ወቀሳ *(ወያኔዎችና መሰል አገር አፍራሽ ተገንጣዮች ታሪካችንን እና ሊቃውንቶቻችንን "ደብተራ/የነፍጠኛ ታሪክ ጸሃፊዎች" እያሉ ዛሬ እንደሚያንኳስሷቸው የዘመናችን "ክፍት አፍ ማይሞችን" ማለት ነው። ከኔው/ጌታቸው ረዳ የታከለ አስተያየት*) ለረዢም ጊዜ ሲቀርብ ቆይቷል። ችግሩ የቀድሞ ታሪካችንን ከግዕዝ ወደ አማርኛ (ወይም ወደ ሌላ ቋንቋ) ተርጉመው ካቀረቡ ጸሐፊዎች እንጂ ቀደምት አባቶቻችን ሃይማኖታዊም ሆነ ሳይንሳዊ ሥራዎቻቸውን ትተውልን አልፈዋል። አባቶቻችን ከሃይማኖት መጻሕፈት በቀር ምርምር ነክ ጽሑፍ አልተውልንም የሚለው ወቀሳ ለረዢም ጊዜ ሲያሳስበኝ የቆየ ጉዳይ ነበር። ወቀሳው እውነት ያለው መሆኑን አለመሆኑን ለማጣራት በማስረጃ የተደገፈ ሀሳብ ለማቅረብ በማሰብ ከሃያ ሁለት ዓመታት በተለያዩ የአገሪቱ ገዳማትና ቤተክርስትያናት በመዘዋወር ጥንታዊ የግዕዝ ጽሑፎችን መርምረያለሁ። በመጨረሻም በቀደምት አባቶቻችን ላይ የሚቀርበው አስተያየት ሰፊ ምርምር ካለማድረግ የመነጨ እንደሆነ ለማረጋገጥ ችሏል። አዘጋጁ በረዢም የምርምር ዘመኑ ያገኘውን ለማካፈል በማሰብ ይህን መጽሐፍ ለማዘጋጀት በቅቷል።" ....ካሉ በኋላ፤ ከተለያዩ ጦርነቶች፤ከዝርፊያ እና ከቃጠሎ ውድመት የዳኑ ስለ መረመሯቸው የግዕዝ መጻሕፍቶች እንዲህ ይላሉ

"በብራና ላይ የሰፈሩ ጽሑፎች ብዙ የእውቀት ክምችት የያዙ ናቸው። በተለያዩ ቦታዎች ብልሽት ሳይገጥማቸው የሚገኙ አስደናቂ ቤተ ክርስትያናትና ቤተ መንግሥቶች ውስጥ የተቀመጡ የግዕዝ መጻሕፍት ባዷቸው አይደሉም። በዘመኑ የነበሩ የግብር አከፋፈል፤የሰላም ዘበኛው ትምህርት፤የሰላማዊ ሰልፍ ሥርዓት ምን ይዘት እንደነበረው፤ሥነ ፍጥረትን በተመለከተ የከዋክብት

አሰፋፈርን፤የምድር ጥልቀትን፤የፀሐይና የጨረቃ ምስጢርን፤የዝናብ ጉዞና ጥናትን፤የመብረቅ ነጎድጓድ፤ የእሳት ወላፈንን የቅመማ ቅመም መድሃኒቶችን የተመለከቱና የመመራመሪያ ምንጭ የሚሆኑ በርካታ ሥራዎች ይገኛሉ። ከዚህ በተጨማሪ የሰላምና የጥበቃ ሃይል (ዛሬ ፖሊስ ብለን የምንጠራው አደረጃጀት ሥልጠና እና ሥራውን የሚገልጹ በርካታ ጽሑፎች አሉ።"

በማለት ቀደምት ወላጆቻችን እና ነገሥታት፤ደራሲያን ጦረኞች፤ሰአሊዎች፤ እናቶች እህቶች፤ጎልማሶች ሁሉ በነበሩበት ዘመን ኢትዮጵያን በልዩ ማሕደር እና ሕንጻ አንጸው እንዴት እንዳስረከቡን በተጋድሎ መዛግብቶቻቸው ተዘርዝረው ያገኛቸውን ያልተነኩ/እስካሁን ድረስ ያላወቅናቸው ታሪኮችን በዚህ ደንቅ ስራ አስፍረውልናል።

ደራሲው በየገዳማቱ ያገኙትን መረጃ ከንጉሥ ሰብታህ ዘመን ጀምሮ እና ከዚያም በፊት በጽሑፍ መረጃ የሕዝብ እና የአገር አስተዳዳርና አጠባበቅ እንዲሁም በሕዝብ ተሳትፎ የተመሰረተ "ቅራት" (በዛሬው አጠራራር ፖሊስ/) የተባለ የሕዝብ ሰላም እና ዳር ድምበር ጠባቂ እንዲሁም ተዋጊና "ሐሰሴ ፍትሕ" (ፍትሕ አስፈጻሚ ሃይል) ተመስርቶ ኢትዮጵያ ትደዳር እንደነበረች፤ በተያያዥም ከክስርቶስ ልደት በፊት በተለያዩ የነገሥታት ዘመን "ፍትሃዊ" አስተዳደር የቀየ የኢትዮጵያዊያኖች ሥራ እንደነበርና እንደየ አካባቢው እና እንደየ ዘመኑ የስሙ አጠራር ሲለዋወጥ እንደነበረ በሰፊው አትተዋል። ባንዳንድ ዘመን ነገሥታት አሰራሩ እጅግ አስገራሚ እና 'ፍትሃዊ'/ አሁን /ዲሞክራሲያዊ/ አሰራር የምንለው አፈጻጸም ሲካሄድ እንደነበር በመረጃ አቅርበዋል። አብዛኛዎቻችን ኢትዮጵያን እና ሊቃውንቶቿ ነገሥታቶቿና ሕዝቧ ታሪኳን እናውቃታለን የምንል ካለን ምንም የማናውቃት መሆናችንን ይህ መጽሐፍ ካነበብን በኋላ ምንኛ መንገድ የሳትን ትወልዶች እንደሆንን መረዳት ይቻላል።

መጽሐፉ "ከፍልስፍና ሊቃውንት የቀረበ ምርምር ፤ከጥበቃ፤ከስለላ፤ከበጐ አድራጐት (ድሆችን ሰብስቦ መቀለብ)፤ከመደሃኒት ቅመማ ፤የሌባ አያያዝ ዘዴ ('ሻይ ሌባ' በሚባል መድሃኒት፤ሌባ/ወንበዴ (ኮረኮሬ ይሉት ነበር በዘመናቸው) በመጠቀም እንዴት ሌባውን ይይዙት እንደነበረ ያትታል። ባለስልጣኖች በሕዝብ ላይ ሲባልጉ/ጉቦ (ኮራብሽን/ንቅዘት የምንለው) የመሳሰሉት ተግባራት ሲፈጽሙ በሕዝቡ ብይን ይቀጡ እንደነበር እና ፤ አንድ ዜጋ ተበደልኩኝ ብሎ አቤቱታ ለማቅረብ ሲፈልግ ነገሥታቱ ጋር ፊት ለፊት ቀርቦ ጉዳዩን የማስረዳት መብት እንደነበረው (እንደማይከለከል) የተለያዩ ዘመናት ነገሥታት አስራር በመረጃ እና ከነደራሲው ስም ዘግበው ከግዕዝ የተረጎሙት ቅጅ በመጽሐፉ ውስጥ አቅርበውታል።

በመጽሐፉ የቀረበው ሰነድ የነብዩ ሙሴ ታሪክ (ላስታ/አማራ/አንጐት ሲባል የነበረው - ኦሮሞዎች አካባቢውን መስፈር ከጀመሩበት በኋላ "ወሎ" የተባለው)

ከነልጁ እና ከሚሰቱ ያሳለፋቸው መንደሮች፤ እና ወደ ተለያዩ መንደሮች (ክፍለ ሃገሮች) የሄደባቸው ጉዞዎች ታሪኮች ከማተቱ ጀምሮ አስደናቂ የኢትዮጵያ ጦረኞች እና ታሪኮችን ይገልጻል። ጠይሚቷ ኢትዮጵያዊት ሚስቱ እስራል ድረስ ከእርሱ ጋር ሄዳ የእስራኤሎቹ (የሙሴ እህት እና ወንድም) ዘረኝነት ተቋቁማ የፈጸመቺው አኩሪ የዘረኝነት ገድል የመቋቋም ገድሏን ያትታል።

እንዲሁም አሰቃቂውና የቱርኮች ቅጥረኛው የግራኝ አህመድ የጥፋት ጦርነት ( "በኢትዮጵያ ምድር የሰውና የጋኔን ጦርነት" በሚል ርዕስ በግዕዝ ጽፎ የተወልንን  በውቅቱ በጦርነቱ ውስጥ እራሱ የተካፈለ የዓይን ምስክርነቱን መዘግቦ የተወልንን ኢትዮጵያዊው የዘመኑ ጻሐፊ "አፈርሳታ" የተባለው የቤተ ክህነት ምሁርና ደራሲ በጦርነቱ የተካፈሉት አለቆች እና ተራ ተዋጊዎች የሰዎቹ ሰም ዝርዝር የተወለዱበት መንደር፤ድፍረታቸው፤ጉብዝናቸው፤ የንጉሥ ልብነ ድንግል ጠጅ ቤት ሃላፊ የነበረቺው "ብርቄ" የተባለቺው ግራኝን ለመሰሰል ተልካ  "ዘይነባ" ተብሎ ስሟ የተለወጠው የፈጸመቺው የስለላ ተጋድሎና አህመድ የተባለው የግራኝ ሃይለኛ ጦረኛ ግራኝ በሰጣት ሰይፍ (የግራኝ የጭን ገረድ፤ታማኝ አገልጋይ ሆና ለስለላ የገባች አርበኛ)  ተኝቶ እንዳለ  እንዴት እንደገደለቺው አስገራሚ ጀግንነቷ እና ሌሎቹም አበባ ሳህሉ  ወዘተ...የመሳሰሉ እንዲሁም  "ተፈራ"  የተባለ የወቅቱ የሰላም ዘበኛ ባለቤት የነበረቺው "እቴቴ የከቲ" የተባለቺው  የሴት አርበኛ  እና መሰል ጓደኞቿ በበርበሬ ሳይቀር የግራኝን አዛዦች  አይን በእሳት ረመጥ (ፍም) ጥምጣማቸው ላይ እና አይናቸው ላይ እየበተኑ የጨበጣ ውግያ እንዴት እንደተዋጉት እና አነ ሐጎስ አብርሃ የተባሉ ጀግኖች ንጉሥ ልብነ ድንግል እጁ እንዳይያዝ ግራኝ ገትረው በመያዝ በከባድ ጦርነት በተራራ ውስጥ ላይ እንዴት አሾልከው እንዲያፈገፍግ እንዳደረጉ አርበኝነታቸውን "አፍረሳ"  የዘገበውን ከግዕዝ ወደ አማርኛ የተረጎሙትን ቀርቧል።

አሳዛኙ ደግሞ  ለአገሪቱ እና ለሕዝበ ክረስትያኑ መታረድ፤እና ጥንታዊ ቅርሶች መጻሐፍት ንብርት ውድመትና የሰላም መደፈርስ ምክንያት የሆነው ለግራኝ ክፍት ዕድል የሰጠው በዘመኑ የነበረው "ንጉሥ ልብነ ድንግል" እንዝህላልነት እንደነበረ በወቅቱ የነበረው ደራሲ (አፍራሳ "በኢትዮጵያ ምድር የሰውና የጋኔን ጦርነት" የሚለው በ15ኛው ክፍለዘመን የደረሰው ደራሲ) ገልጿል። ካገር ሽማግሌዎች እና ከሰራዊት አዋጊዎች ሲሰጠው የነበረውን የተመከረውን የውጊያ ስልትና  የቱርኮች ጣልቃ ገብነት ፤የግራኝ ቅጥረኛነት እውን መሆኑን ቢነገረው ማስጠንቀቂያው ቸል እያለ አልሰማችሁም እያለ ቁጭ ብሎ በየቦታው ድግስ ሲያስደግደስ መጨረሻ  ግራኝ እየተዘጋጀ እያለ እንዝህላልነት በማሳየቱ ለጥቃት ተዳረጓል።

አፍራሳ የውግያ ዝግጅት በሚያስጎመጅ፤በሚያሳዝን በተለያዩ ስሜትን በሚነዝር አቀራረብ የቀረበው የጥንቱ ዘጋቢ ሰነድ ተተርጉሟል። አያይዘውም  "ነግሥት

ኒካውላ ቅንደኬ” (በግዕዙ አጻጻፍ ቅንደኬ እንጂ ክንደኬ አይደለም ይላሉ ደራሲው) ጊዜ የግሪኩ ተወላጅ ታላቁ እስክንድር ግብፅን እንደያዘ ኢትዮጵያን ለመውረር እንደማይመለስ ንግሥቲቷ ተጠራጥረው ስለነበር ፤ እራሱ ተራ መንገደኛ ተመስሎ ወደ ኢትዮጵያ ገብቶ ስለላው ለማካሄድ ሲገባ ኬላ/ድምበር ላይ በንግሥቲቱ ትእዛዝ በወቅቱ ዘመን በእጅ ስዕል የተካኑ ሰአሊዎች የእስክንድርን ምስል ስለው በየኬላው በትነውት ስለነበር “የስለላ ክፍሉ” (ፈረሰኛ አገር ጠባቂ ሠራዊት ሲባል የነበረው) ‘ቅራት’ (ፖሊስ....) እስክንድር ሾልኮ ለመግባት ሲሞክር ተይዞ ወደ ንግሥቲቱ ቀርቦ ፤ንግሥቲቱ እራሳቸው “ምርመራ እንዳካሄዱበት” እሱንን በቤተመንግሥት በክብር ተይዞእንዲቆይ እና አብረውት የነበሩትን እንደየ ደረጃ መአረጋቸው ተበታትነው እንዲታሰሩ እና ዝቅተኛ ሹሞቹም በወቅቱ በግዕዙ “ሠራኤ” ተብሎ ሲጠራ የነበረው ዛሬ “ሰራዬ” የሚባለው ኤርትራ አውራጃ ውስጥ ተወስደው ታስረው እንደነበሩ እና ፤ መጨረሻም በክብር ተለቅቆ ወደ መጣበት ግብጽ እንዲሄድ መደረጉን “ዜና እስክንድር ከገጽ 300-605፤ ላስታ፤ጀምቦ ማርያም፤ በተባለው ገዳም/ቤተክርስትያን የተገኘው ጥንታዊ እጅግ አሮጌ የግዕዝ መጽሐፍ ያተተውን ታሪክ ዘግበውታል።

ለምሳሌ ኤባል የተባለ ኢትዮጵያዊ ንጉሥ ነገሥት እንዲህ ሲል የጻፈው አዋጅ በመጽሐፉ መግቢያ ያወጀውን በእንዲህ ተተርጉሞ ቀርቧል።

<<እኔ ኤባል ስመ መንግሠቴ ሰብታህ እጅግ ገናናነቴንና ለሕዝብ አሳቢነቴን ዓለም እንዲያውቀው፤የማስተዳድረው የኢትዮጵያ ኩሽ ሕዝብ ንብረቱ እንዳይባክን፤ሲሠራ ውሎ ሌሊት ለጥበቃ እንዳይዞር ሕጉን የሚያስከብርለትን የሌሊቱን ሆነ የቀኑን ኮረኮሬ/ወንበዴ/ የሚይዝለት፤ የሚያስርለት በተለይ ለሕዝብ መብት ጠባቂ የሚስማማ፤የሠራዊት አቋቋምኩ። ስሙም መሪ ፈረሰኛ አገር ጠባቂ እንዲባል አዝዣለሁ።

ሕዝብ ሆይ!
ከእንግዲህ ወዲህ ከመሪ ፈረሰኛ አገር ጠባቂ ሠራዊት በቀር ገበሬው ሕዝብ፤ ማረስና መብላት፤ለመንግሥት የሚገብረው ክምርቱ ከአሥር አንድ በቀር ሌላ የሚፈለግበት የለም። አሶርያውያንና ፍልስጥኤሞች /ፓልስታይኖች/ የድንበር ማለፍ የሚቋቋመው ይኸው መሪ ፈረሰኛ አገር ጠባቂ ሠራዊት ነው። የሕዝብን ፀጥታና መብት የሚያስከብረውም ይኸው ሠራዊት ነው። እንዳለፈው ጊዜ ገበሬ ለሰላም ጥበቃ ሆነ ለጦርነት አይወጣም።>>

( ንጉሥ ሰብታህ ስለሰላም ጠባቂ መቋቋም ያወጣው አዋጅ)።

እንግዲህ ኢትዮጵያ (የኩሽ ሕዝብ) እንዴት ያለ የሰለጠነ አስተዳደር ትከተል እንደነበረ የተጻፉ መዛግብቶች ያመለክታሉ። የወቅቱ ጦረኞች ፍልስጤሞች ፤ አሶርያውያን ድምበር የኢትዮጵያን ኬላ/ደምበር እንዳይጥሱ የሚቋቋም ሠራዊት

ራሱ የቻለ ተዋጊ ዘርፍ እንዴት ተዋቅሮ ሥራ ላይ  ውሎ ሰላምና ሉአላዊነት ይጠበቅ እንደነበረ መረጃዎቹ ያመላክታሉ።

የቱ ከየትኛው ታሪክ መርጦ ለመዘገብ አስቸጋሪ ቢሆነኝም፤ ለናንተ ለማካፈል የፈለግኩት ዛሬ ወያኔ በማያውቀው የዲሞክራሲ አመሰራረት ታሪክ ጥልቅ (ከረር ብሎ ይነበብ) ብሎ በማያውቀው ጉዳይ ሳያፍር "ዲሞክራሲ ለመጀመሪያ ጊዜ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አስተዋውቄአለሁ" በማለት አስቂኝ ንግግሩን እና ውሸቱን ምን ያህል እንደሆነ ታሪካችንን ለመመርመር ያመቸን ዘንድ መጽሐፉ ማንበብ ጠቃሚ ቢሆንም፤ ሌላ ቀርቶ በዘመነ ዳዊት የሕዝብ ድምፅ ይሰማ እንደነበረ እና ሕዝቡ ቅሬታውን "ሰላማዊ ሰልፍ" እንዴት እንዲገልጽ በሕግ ተደንግጎ ይፈጸም እንደነበረ አንዱን ክፍል መርጬ ላቅርብላችሁ።

የወያኔ መሪዎች እና አሳፋሪ ጀሌዎቻቸው የኢትዮጵያን ነገሥታት እና ታሪክ ጸሐፊዎቻችን (አማራ/ደብተራ/ነፍጠኛ/የመንደር ወሬ ጸሓፊዎች... እያሉ ) መዝለፋቸውን ያቁሙና "ዝምብ እየገባበት ያለው ክፍት አፍ ማይምነታቸውን" ለማስወገድ ታሪክ የዘገበልን ፊደል ቆጣሪ ገብተው ራሳቸውን ለማሳደስ ፍላጐት ካላቸው ወላጆቻቸውንና የአገሪቱን ጠበል ከማደፍረስ ይቆጠቡ።

ዲሞክራሲ ከግሪክ መጣ የሚሉት  ሞኝ ምሁራኖቻችንም  ያገራችንን ታሪክ "ሀ" ብለው ተምረው "ሕዝባዊ ሥራ አና ተሳትፎ" ከግርክ የመጣ ሳይሆን "ኢትዮጵያዊ ነው"። ባይገርማችሁ "ግዕዝ" የመጀመሪያው የዓለም ቋንቋ ሆኖ እንዴት እንደተጀመረ እና እየተዋጠ እንደሄደ የግዕዝ መጽሐፍት ደራሲዎች አብራርተዋል። እንዲህ ሲባል የማይዋጥላቸው የባሕር ማዶ ቋንቋ 'የላቲንና ዓረብኛ ፊደል' አወዳሾች የሆኑት 'ወያኔዎች፤አነጐች፤አረቦች ነን የሚሉ ኦጋዴን ሶማሌዎች፤ሲዳማዎች...ወዘተ....ወዘተ....) አይዋጥላቸውምና፤ በክሕደት ላይ ያለ ሕሊናቸወውን ለመፈወስ "ሌባ ሻይ" የተባለው የጥንቱ ፈውስ ቢገኝ ጥሩ ነበር።

አሁን ወደ ታሪኩ ልወሰዳችሁ።

የቀዳማዊው ንጉሥ ዳዊት ታሪክ የተጻፈበት ዘመን እና መጽሀፍ ደራሲው ያገኙት ምንጭ (*"መምህር ዘጎንደር፤ኢትዮጵያዊው ቀዳማዊ ዳዊት፤ ሙብተ ሕዝብ፤በግዕዝ ልሳን፤ገጽ 109፤የመጽሐፉ መገኛ ዋድላ ወዳት ቂርቆስ፤909 የተጻፈበት ዘምን፥ የመጀመሪያው። ጸሐፊው ጎይቶም የቀርነ ማርያም አሊቃ። )* ሰለ ሰላማዊ ሰልፍ አፈጻጸም፤ሕዝቡ በትከሻው፤ በራሱ በደረቱ፤ በክንዶቹ፤ በጣቶቹ እጆቹ ላይ ምን ይዞ፤የተለያዩ ዕቃዎች ተሸክሞ፤ጨብጦ ሰላማዊ ሰልፍ በመውጣት ንጉሡ ዙፋን ፊት ቀርቦ  አቤቱታውን እና በንጉሡም ሆነ በሕዝብ አገልጋዮች ላይ የሚቀርብ ቅሬታ ማሻሻያ ወይንም ክስ ካለ በሰላማዊ ሰልፍ የወጡት ሰልፈኞች ንጉሡ ከዙፋኑ ቆሞ ደምጻቸው እንዴት በክብር ያዳምጥና

ይደመጥ እንደነበር በ909 የተጻፈው የመምህር ዘጎንደር "መብተ ሕዝብ" መጽሐፍ ትርጉም ያቀረቡትን በቅንጫቢ መልክ እንዲህ ሲሉ ያቀረቡትን እነሆ። ሐተታው በክፍል ሁለት ይቀጥላል...... (ጌታቸው ረዳ - የኢትዮጵያን ሰማይ ድረገጽ አዘጋጅ)